Saturday, 05 December 2015 09:00

# አስከፊው የድርቅና ረሃብ ታሪካችን

ተሾመ ብርሃኑ ከማል



-
-
- **"**ረሃብ**"** የሚለውን ቃል ስንሰማ ከብዙ ሁኔታዎች ጋር ልናያይዘው እንችላለን፡፡ የተለያዩ አገራት ሕዝቦችም ስለ ረሃብ አንድ ዓይነት አመለካከትና ትርጉም አይኖራቸውም፡፡ ከተሜዎችና ገጠሬዎችም እንዲሁ። ሕጻን ይርበዋል፤ ያለቅሳል፤ ሲያለቅስ ይሰጠዋል፡፡ ዝም ይላል፡፡ አዋቂም ባያለቅስም በተወሰነ ጊዜ ምግቡን ካላገኘ ይራባል፡፡ ነገር ግን ከድርቅ ጋር የተያያዘው ረሃብ፣ ከተራው ረሃብ ይለያል፡፡ በድርቅ ምክንያት የሚመጣው ረሃብ፣ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን ያስርባል፡፡ ቁርስ እየቀረ በምሳና በራት መዋል፡፡ ቀጥሎም ቁርስና ምሳ ወይም እራት እየቀረ በአንድ ምግብ መዋል፡፡ የአንድ እለት የምግብ መጠን እየቀነሰ መሄድና መታጣትን ያስከትላል፡፡ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ፤ የድርቅና የርሃብ ሰለባ ከሆኑ ወገኖቹ ጋር በ **1955**፣ በ **1957**፣ በ **1977** በሰቆጣ፣ በኮረም፣ በመቀሌ፣ በአዲስ አበባ እንዳየው፤**...** ለአንድ የአገራችን ገበሬ ረሃብ ማለት ዝናብ ባለመጣሉ ምክንያት መሬት የዘሩባትን ሳታበቅል ስትቀር፣ በዚህም ሳቢያ በእረኝነት የተሠማሩ ልጆች በፀሐይ ሐሩር የተቀላውን ከታረሰው ማሳ እየለቀሙ ሲበሉ፣ ወንዞችና ምንጮች የተደፉ ቡሃቃ ወይም ሊጥ የፈሰሰባቸው መስለው ሲደርቁ፣ በጥልቀት ቢቆፈሩ እንኳን እንጥፍጣፊ ሲታጣባቸው፣ ላሞች በጎችና ፍየሎች ወተትም ሥጋም ቆዳም የማይገኝባቸው ሲሆኑ አስቀድመው ግልገሎቻቸው፣ በኋላም እራሳቸው ማለቅ ሲጀምሩ፤ ትንሽ አቅም የነበራቸው የመጨረሻዎቹ እንስሳት በየበረታቸው ውስጥ ጣረሞት ይዟቸው እየተንፈራፈሩ ሲሞቱ፣ በዚህም ምክንያት በቅድሚያ ከቤተሰብ ደካሞችና በሽተኞች በያሉበት ሲሞቱና በአንድ መንደር ውስጥ በቀን ከአምስት ስድስት ጊዜ በላይ የአቃብሩኝ ልፈፋ ወይም ጥሪ መሰማት ሲጀምር፣ ከዚያም ጠንካሮቹ እየደከሙ ወደማይቀረው የዘላለም ቤታቸው ሲጓዙና ቀባሪ አጥተው በየቤት ሲቀሩ፣ ቀዬውንና አካባቢውን ትቶ ሕዝብ መሰደድ ሲጀምር **----** ያኔ ርሃብ መጥቷል፡፡

እስቲ ከራሴ ልምድ ላካፍላችሁ፡፡ በ **1950** አካባቢ በዋግ ኸምራ ዞን ርሃብ ይከሰታል፡፡ የሚሸጥና የሚለወጥ እህል ይጠፋል፡፡ ገበሬ ለራሱም ስላልነበረው ማምጣት አይችልም፡፡ ከትግራይና ከበለሳ እንዳይበደር እዛም ድርቅ ሆነ፡፡ ትንንሽና ትልልቅ ወንዞች ደረቁ፡፡ የተዘራው የጓሮ በቆሎ፣ አተርና ባቄላ በቅሎ ቀረ፡፡ ዱባ አላፈራም አለ፡፡ በሐምሌና በነሐሴ ይበቅሉ የነበሩ ቅጠላ ቅጠሎች ከመሬት ብቅ እንዳሉ ቀሩ፡፡ ፍየሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እከክ ጨረሳቸው፡፡ ሰው እንኳን ሊበላቸው በማያስችል ፍጥነት አለቁ፡፡ ትንሽ ለምልሞ የታየው ዱባም ቢሆን አላፈራ አለ፡፡ ያፈራውም አልፋፋ አለ፡፡ እና ምን ይደረግ**?** ለጊዜ በቤታቸው የተገኘው ጥፍጥሬ ነበር፡፡ ጥፍጥሬውን እየቀጠቀጡ ከውስጡ ያለውን ነገር እያበሰሉ በሙቅ መልክ መጠጣት፡፡ እሱም ለእራት ብቻ ነበር የሚገኘው። ዱባ ከብርቱካን መጠን በላይ ሊጨምር ባለመቻሉ የተቀቀለ መብላት ተጀመረ፡፡

ሌላ ጥሬ ወዳለበት አካባቢ ተኪዶ እንዳይገዛ የሸማኔውን፣ የልብስ ሰፊውን፣ የአንጥረኛውን፣ የማረሻ ሠሪውን፣ የቅመማ ቅመም ነጋዴውን  ምርት የሚገዛው ገበሬ ተርቦ ስለነበር ገንዘብ የለም፡፡ ስለዚህ እልቂት ሆነ፡፡ አንገታችንና ከአንገታችን በታች ያለው አካል እንደ ሽምበቆ እየቀጠነ መጣ፡፡ ጎላ ብሎ የሚታየው ጭንቅላታችን ሆነ፡፡ ረሃብ ግን በዚያ ጊዜ ተጀምሮ በዚያው አላበቃም፡፡ ግን ርሃብ ሲይዝ ምን ይመስላል**?** ከየትኛውስ ጊዜ እንጀምር**?** ረሃብን  ለማታውቁ እነሆ**!**

የረዥም ዘመኑን ረሃብ ለጊዜው እናቆየውና የዛሬ መቶ ዓመት አካባቢ በኢትዮጵያ ስለደረሰው ድርቅና ረሃብ በተለይም በፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንከረስት መጽሐፍ የሰፈረውን ስንመለከት፣ በኢትዮጵያ ከደረሱት በጣም ትልቅ የድርቅና የረሀብ ዘመናት አንዱ ከ **1888-1892** ማለትም አጼ ዮሐንስ በሞቱበት ጊዜ የነበረው መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ በዚህ ጊዜ የነበሩት የሮም ሚሲዮኖች  እንደመዘገቡት፤

የአየሩ ሁኔታ ባልተለመደ መልኩ ሞቃት ሆነ፡፡ ይህም የአየር ንብረቱን አዛባው፡፡ እንደ ሰደድ እሳትም መላውን ምድር አጥለቀለቀው፡ የአየር ንብረቱ መዛባት ለሱማሊያና ለደቡባዊ አገሮችም ተረፈ፡፡ በወቅቱ ኢትዮጵያን የጎበኘ ማርቲ የተባለ ግለሰብ ስለ ድርቁ ሲገልጽም፡-

‹‹በቆሻሻ ጨርቅ የተሸፈነ ሬሳ እዚህም እዚያም ወድቆ ይታያል፡፡ በዚያ ሐሩር ፀሀይ ላይ ወድቀው ከሚታዩት አስከሬኖች ክንዶችና እግሮች ላይ ነፍሳት ሲርመሰመሱባቸው ማየት እጅጉን ያሰቅቃል፡፡ በሕይወት ያሉት ሞታቸውን ሲጠባበቁ፣ የሞቱት ደግሞ የሚቀራመቷቸውን ጅቦች ይጠብቃሉ፡፡ በየሥርቻው የሚሰቃይና የሚያቃስት ድምጽ ይሰማል፡፡ ሥጋው አልቆ በቆዳው የተሸፈነ እጅ እስከ መጨረሻዋ ትንፋሽ መውጣት ድረስ አለሁ ለማለት የፈለገ ያህል ይላወሳል፡፡ እዚህም እዚያም ለሞት የተቃረበ ሰው በመጨረሻ እንቅስቃሴ እያጣጣረ፣ ቀስ በቀስ ቀና ብሎ እንደ መቀመጥ ይቃጣውና ሞጭሙጭ እንደ መስታወት በሚብለጨለጨውና ነፍስያ እንደሌለው በሚያስታውቀው ዓይኑ እንደ መማተር ይላል፡፡ የማይሰማ በከንፈሩ ብቻ የሚላወስ ቃል እንደ ማነብነብ ይልና ቀጭን ድምጽ አሰምቶ ዝልፍልፍ ብሎ ይወድቃል፡፡ ከዚያም ጭጭ ይላል፡፡

"በጠኔ የተጎሳቆለች እናት መናገር አቅቷት፣ ሕጻን ልጇን እያወዛወዘች ምስኪን ነኝ፣ ምስኪን፣ እያለች ላመል ያህል በሚሰማ ቆርፋዳ ድምጽ ምፅዋት ትለምናለች፡፡ የኛን እርዳታ የሚፈልጉ ብዙ አፅም የመሰሉ ፍጡራን አጋጥመውኛል፡፡ ምስኪን ነኝ እያሉ እየተውተረተሩ፣እየተነሱ እየወደቁ ያቅማቸውን ያህል ለመከተል እየሞከሩ ምፅዋት ይጠይቁናል፡፡ ሴቶች እኛን ሲያዩ ጨቅላዎቻቸውን ከመሬት ብድግ አድርገው፣ የደረቀና የሚሸሽ ጡታቸውን በእጃቸው እያሳዩን በለቅሶና በዋይታ እየለመኑ ይከተሉናል፡፡ አንዳንዴ ሊሬ ጣል እናደርጋላቸዋለን፡፡ ነገሩን አሁን ሳስበው፤ ከአንድ ሰዓት በላይ ዕድሜ ለማይኖራቸው ረሃብተኞች ገንዘብ መስጠት ምን ዓይነት ትርጉም የለሽ ሞኝነት ነው እላለሁ። እንዲህ ያለውን ሳይና ከአካባቢው ለመሸሽ ስደናበርም ዓይኖቼ ከግመሎች ዓይነ ምድር ፍራፍሬ እየፈለጉ ከሚለቅሙ ትንንሽ ልጆች ጋር እየተጋጩ እቸገራለሁ፡፡ ከእንዲህ ያለው አስቀያሚ ትዕይንት ለማምለጥ ስሞክር፣ ዘበኞች ከሞተ ፈረስ አጠገብ፣ አሞሮችን ሲያባርሩ እመለከታለሁ፡፡ ልጆቹ ከጅብ የተረፈ የፈረስ አንጀት  ለስላሳ ስለሚሆንላቸው በጥርሳቸው ይገዘግዙታል፡፡ በዚህ ጊዜ ከማየት በስተቀር በሰቀቀን ምንም ለማድረግ ባለመቻሌ እየተደናበርኩ ከአካባቢው በረሀ ጥፋ የሚል ግፊት ይመጣብኛል፡፡ የተንጠለጠለውን የኪሴን ሰዓት ወርውር ወርውር ያሰኘኛል፡፡ ጧት የበላሁትን ቁርስና የሚጠብቀኝን ምሳ ሳስብ በራሴ ላይ እፍረት ይሠማኛል፡፡" ብሏል፡፡ (ትርጉም መስፍን ሀብተማርያም)

ድርቅና ረሃብ መቼ ተከሰተ? ምንስ ጥፋት አደረሰ?

እንዲህ ያለው ድርቅ የተከሰተው ከ **1888-1892** ብቻ አልነበረም፡፡ እንደ ማርቲን ያለ ጸሐፊ አያጋጥመው እንጂ በኢትዮጵያ የረሃብ ታሪክ ማህደር ሰፍሮ እንደምናገኘው÷ ከ **1131-1145**፣ በ **1258**፣ በ **1261**፣ በ **1262**፣ በ **1274** ረሃብና በሽታ ደርሶ ነበር፡፡ ሆኖም መንስኤዎቻቸው እንደ አየር ንብረት መዛባትና ሰው ሰራሽ ችግሮች ሳይሆን እንደ ፈጣሪ ቁጣና አንድም ሕዝቡ ለንጉሦች ባለመታዘዙ ወይም ንጉሦች የተሰጣቸውን መለኮታዊ አደራ ባለመወጣታቸው እንደተከሰተ ተደርጎ ሲጠቀስ ቆይቷል። ስለዚህም ጉዳይ የታሪክ ጸሐፍቱ ሲገልጹ፡-

"እግዚአብሔር የረሱትን መንግሥታት በበሽታ፣ በረሃብና በጦርነት ይቀጣል፡፡ እነዚህ መንግሥታት እውነተኛውን እምነትና የተቀደሱ ሕጋቱን ትተው በሐሰት ስለሚበከሉ የጥፋትንና የእግርማንን መንገድ የሚከተሉ ናቸው" ይሏቸዋል፡፡

በተለይም ከ **1315-1344** በነበረው የአጼ አምደጽዮን ዘመን መንግሥት እጅግ አስከፊ ድርቅና ረሃብ እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህንንም የድርቅ ዘመን አቡነ አሮን የተባሉ በቤጌምድር የነበሩ ቅዱስ ሰው፤ በአምደ ጽዮንና በሰይፈ አርአድ ዘመነ መንግሥት **(113-1372)** በተከሰተው ድርቅ፣ ረሃብና በሽታ በመላው ኢትዮጵያ ተስፋፍቶ እንደነበር ያወሳሉ፡፡ ያኔ ከአቡነ አሮን ተማሪዎች ብቻ **1400** ሞተው ቤተክርስቲያኗን ሞልተዋት ነበር፡፡

የደብረ ቢዛን (ትግራይ) ገዳም መነኩሴ የነበሩት አባ ዮሐንስ (በኮንቲሮዝ ግምት ከ **1369-1448)** ባለው ጊዜ ድርቅ በገዳሙ እንደተከሰተና የገዳሙን መነኮሳት እንደጨረሳቸው ጠቅሰዋል፡፡

በ **15** ኛው ክፍለ ዘመን የደረሰውን የረሃብ እልቂት በተመለከተ የተጠናከረ መረጃ ባይርም አል-ማግሪቢ የተባለ የአረብ ታሪክ መዝጋቢ፣ በአጼ ዘርአያቆብ ዘመነ መንግሥት **(1434-1568)** በተለይም ከ **1434-6** በነበረው ጊዜ ብዙ ህዝብ እንደ ፈጀና በመላው አገሪቱ የህዝብን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንደቀነሰ ዘግቧል፡፡

ከ **1508-1540** በነበረው የአጼ ልብነድንግል ዘመን መንግሥትም በዝናብ እጥረት ምክንያት በርካታ ሰዎች አልቀዋል፡፡ ከአጼ ልብነድንግል በኋላም በተለይም በአጼ ገላውዲዮስ ዘመነ መንግስት **(1540-1569)** ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ ቸነፈር ደርሶ ነበር፡፡ በ **1611** ማንንትታ፣ በ **1683** ለባብል፣ በ **1693** ታናካ የተባሉ በሽታዎች ብዙ ሕዝብ ጨርሰዋል፡፡

በአጼ እያሱ ዘመን መንግሥት በተለይም በ **1706** የደረሰው ረሃብ፣ የጎንደርን ህዝብ ከዚህ መቅሰፍት አድነን በማለት ንጉሠ ነገሥቱን እንዲማፀን አድርጎታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በ **1747** እና በ **1748** በተከታታይ አንበጣ ሰማዩን እንደ ጉም ይሸፍነው እንደነበርና ይኸም ክፍተኛ ቁጥር ያለው የአንበጣ መንጋ የቆላውንና የደጋውን ሕዝብ ለረሃብ እንዳጋለጠው እንዲሁም ለጉንፋንና ለሌሎችም ብዙ በሽታዎች በመዳረግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ከምድረ ገጽ እንዳጠፋ ይታወቃል፡፡

ከ **1772/73** በነበረው ዘመን ቀጭኔ የሚባል ረሃብ እንደገባ፣ ከ **1750-1769** በምጽዋ በተለይም በሐርቂቆ የተከሰተው ረሃብ ወደ ሌላው የአገሪቱ ክፍል የተስፋፋ ሲሆን ከዚያም ከ **1788/89** መላውን ክልል አዳርሶ፣ በ **1796** ብዙ ወረዳዎችን አጥፍቷል፡፡

በ **1842** ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ቻርልስ ጆንሰን የተባለ እንግሊዛዊ ሐኪም እንደገለጠው፤ ከ **1828-29** በሸዋ ውስጥ አሰቃቂ ድርቅና ረሃብ ደርሷል፡፡ በዚህም ጊዜ ጆይ ኤል ክራፍ የተባለ ሚሲዮናዊ፣ ረሃቡ የወሎን ሕዝብ እንደቅጠል አርግፎ እንደጨረሰው ዘግቧል፡፡ በ **1889** በሸዋ፣ በሱማሌ፣ በከፋና በጅማ **--** በጥቅምት፣ በህዳር፣ በግንቦት ብዙ ሰዎችንና ከብቶችን ገድሏል፡፡ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ቀደም ሲል የተጠቀሰውን **"**ዘ ሂስትሪ ኦቭ ፋሚን ኤንድ ኤፒደሚክ ኢን ኢትዮጵያ ፕሪየር ቱ ዘ ትዌንቲዝ ሴንቸሪ**"** በሚል ርዕሰ ባሳተሙት መጽሐፍ በርካታ የታሪክ መጻሕፍት አጣቅሰው ሲያቀርቡ፣ ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ደግሞ ከዚያ ቀጥሎ ያለውን የረሃብ ዘመን **‹‹**ሩላር ቨልነረብሊቲ ቱ ፋሚን ኢን ኢትዮጵያ**››** በሚል ርእሰ በሳተሙት መጽሐፋቸው በዝርዝር አቅርበውታል፡፡ በመግቢያቸው ላይ ስለረሃብ ምንነት ሲገልጹም፡**-**

**"**ረሃብ የተመሠቃቀለ ትዕይንትን ይፈጥራል። የሕመም ስቃይ ዝቅተኛ መሆንን፣ ተስፋ መቁረጥንና በአንደበት የማይገለጥ ነገር ግን አጥንት በአጥንት ከሆነ ፊት የሚነበብ ውስጣዊ ብስጭትን ያስከትላል፡፡ ረሃብ ለመሞት የብዙ ወራት ጉዞ የሚደረግበት ነው፡፡ ረሃብ የሚታይ ጭንቀት፣ ሰቆቃና ፍርሃት ነው፡፡ ከሰዎች መካከል የታደሉት አይተውት ይሆናል፡፡ ግን ሞት አፋፍ ላይ ያለው ወይም ከእውነተኛው ሞት ጋር ፊት ለፊት የተጋፈጠው በእውን የሚያየውን ያህል አይሆንም። የረሃብን ያህል ሰው በሰው ላይ የሚፈጽመውን ኢ**-**ሰብአዊነት የሚያጋልጥ የለም፡፡ የባህልና የሃይማኖት ዋጋ ግብዝነትና መመጻደቅ እንደሆነ የሚያሳይም ረሃብ ነው፡፡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት አልበኝነት የሚፈጥርም ረሀብ ነው፡፡

**"...** ያለፉትን በሙቶ የሚቆጠሩ የረሃብ ዓመታት በትዝታ ዓይን እያየን እንለፋቸው እንዳንል የአዲስ አበባ ሕዝብ እንኳን ምንነቱን የማያውቀው ረሃብ ትግራይ ላይ በ **1958** ተከስቷል፡፡ በዚያን ጊዜ ረሃቡን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳያውቀው ይፈለግ ስለነበር ለቤተክርስቲያንም ይሁን ለመስጊድ ማደሻ፣ ለመንገድም ይሁን ለትምህርት ቤት ማሰሪያ**....** ብቻ ለምን እንደሆነ ለማያውቀው ጉዳይ ግን መዋጮ እንዲያዋጣ ተጠየቀ፡፡ ረሃቡ በገባ በሶስተኛ ዓመቱም በ **1961** ላይ የአሜሪካ መንግሥት **7.5** ቶን እህል ሲረዳ መቶ ሺህ ያህል ሕዝብ አልቆ ነበር፡፡**"** ይላሉ፡፡

ረሃብ ሲከሰት በሽታም ይከተላል፡፡ ያኔ ፈንጣጣ፣ ተስቦ፣ ከፉኝ፣ ወባ**.....** እና ሌሎችም በሽታዎች ምህረት የለሽ ክንዳቸውን ያሳዩበትና ሕዝብ እንደቅጠል የረገፈበት ጊዜ ነበር፡፡

ድርቁ በአንድ አካባቢ ብቻ አልረጋም፡፡ ወደ ሰሜን ወሎ በተለይም ወደ ዋግና ላስታ ተዛምቶ ሕዝቡን በጭካኔ ረፍርፎታል፡፡ ይህ ረሃብ ከሰሜን ወደ ማዕከላዊ ሀገር ተዛመተ፡፡ ተመሳሳይ እልቂትም ፈጽሞ ወደ ደቡብ ሸዋ ሸምጥ ሸለቆ፣ ሐረርጌ፣ ሲዳም፣ ጋሞጎፋ፣ ኢሉባቦር ፣ወለጋ፣ ጎጃም ተስፋፋ፡፡ በ **1975/77** ደግሞ በድርቅ ተጠቅተው የማያውቁት አርጆ፣ ባህርዳር፣ ደብረ ታቦር፣ ጨቦና ጉራጌ፣ ሳይቀሩ በረሃብ ተወገሩ፡፡ ምንም እንኳን የአጼ ኃ/ሥላሴ መንግስት ረሃቡ በኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም ህዝብ እንዳይታወቅ ለማፈን ቢፈልግም የሚቻል አልሆነም፡፡ በ **121** አውራጃዎች **6,478,760** ማለትም በማዕከላዊ ግምት በየአውራጃው **53,543** ሰዎች ድርቁ ባስከተለው ረሃብ አልቀዋል፡፡ በዚህም ስሌት መሠረት፣ በ **20** ዓመት ውስጥ የረሃብ ሰለባ የሆነው ሕዝብ **25,111,887** ይደርሳል፡፡ የመንግሥት መረጃ ደግሞ በ **63** አውራጃዎች **263,578** እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ይህስ ቢሆን በወቅቱ ደራሽ አጥቶ ታፍኖ ማለቅ ነበረበት**?**

ድርቅና ረሃብ የሚያስከትሉት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች

ከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በፊት በነበሩ መንግሥታት በፈጣሪ ቁጣ ወይም ነገሥታቱን ባለመታዘዝ ወይም በጥጋብ እንደተከሰተ ተደርጎ ሲወሰድ፣ ለአጼ ኃ/ሥላሴ መንግሥት ደግሞ መንኮታኮቻ ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ነገሩ **"**አንበሳን ፈርተው ዛፍ ላይ ቢወጡ ነብር ጠበቃቸው**"** እንደሚባለው ሆነ እንጂ የዚያን ሥርዓት ፈላጭ ቆራጭነት ባህርይም የበለጠ ጉልህ አድርጎታል። ድርቅና ረሃብን በተመለከተ ገና በብዛት መጠናትና መጻፍ ያለበት ቢሆንም ከጤና አኳያ ከተነተኑት መካከል አብርሃ ግዛው የተባሉ ምሁር **‹‹**ኤኮሎጂ ኦፍ ሄልዝ ኤንድ ዲዝዝ ኢን ኢትዮጵያ**››** በሚል ርእስ ዜይን አህመድ ዜን እና ሄልሙት ኩልስ ባዘጋጁት መጽሐፍ **(1988)** ላይ እንዳሰፈሩት፤ ምንም እንኳን ከአብዮቱ በኋላ የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ረሃብ ከመድረሱ በፊት የቅድሚያ ጥንቃቄ አገልግሎት እንዲሰጥ ጭምር ቢመሠረትም ረሃቡ እየተባበሰ እንጂ እየተሻሻለ ሲሄድ አልታየም፡፡ እንዲያውም በወሎና በትግራይ የተከሰተው ዓይነት ረሃብ፣ በ **1977** በኦጋዴንና በባሌ በተለይ በኤልካሬ፣ በኤሊባቦር፣ በተለይም በቡኖ በደሌ፣ በሰሜን ሸዋ ተስፋፋ፡፡ በ **1979** ላይም ከፍተኛ ምርት በማምረት በምትታወቀው በአርሲ፣ በደቡብ ሸዋ፣ በሲዳሞ፣ በጋሞጎፋ ታየ፡፡ በ **1981** ምሥራቅ ጎንደር በድርቅ ተመታ። የድርቁ ጥቃት አይሎ በቀጠለበት በ **1984** ላይ የደርግ መንግስት ከወሎ **367,016**፣ ከሸዋ **108,241**፣ ከትግራይ **89,716**፣ ከምሥራቅ ጎጃም **16.425**፣ ከምስራቅ ጎንደር **6387**፣ በአጠቃላይም **600** ሺ ሰፋሪዎችን፤ በወለጋ **253,282**፣ በጎጃም **101,785**፣ በኢሊባቦር **147,915**፣ በከፋ **72830**፣ እና በምዕራብ ጎንደር **6378**፣ አሰፈረ፡፡ ይህ ግን ድርቁና ረሃቡ የሚያስከትሉትን ችግሮች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊያስቀር የሚችል እርምጃ አልነበረም፡፡

ድርቅና ረሃብን ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት**?**

በመሠረቱ የተፈጥሮ ሰለባ የሆነችው ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን በሳህል በረሃ ውስጥ የሚጠቃለሉት አገሮች በተለይም ሱዳን፣ ናይጀሪያ፣ ማሊ፣ ኡጋንዳ፣ ሞሪታንያና ሌሎችም አገሮች ጭምር ናቸው፡፡ አንድ የጣና በለስ ፕሮጀክት መጽሔት **(1985** አትሙ**)** እንደገለጸው፤ **"**በነዚህ አገሮች በተለይም በ **1977** የደረሰው ድርቅ ባስከተለው የረሃብ ቸነፈር በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ሰዎች ሞተዋል፡፡ የችግሩ ስፋትና ያስከተለው አሰቃቂ ጉዳት መላውን ዓለም ያስደነገጠ፣ የበለጸጉ አገሮች እንዲህ ያለው ጥቃት ለሚደርስባቸው አገሮች

የሚቻላቸውን ድጋፍ ሁሉ እንዲያደርጉ ያነሳሳና ሥር የሰደደውን ችግር በአንድ ጊዜ ለማስወገድ ባይቻልም እንኳን ቀስ በቀስ ለመቅረፍ ሐሳብ የቀረበበት፤ የአፈር መሸርሸር፣ የአየር መዛባት፣ የተፈጥሮ ሀብት በትክክል ለመጠቀም አለመቻል ቴክኖሎጂያዊና ኢንዱስትሪያዊ እንቅስቃሴ እንዲዘረጋ የታመነበት ጊዜ ሆነ" ይላል፡፡

አሰፋ ወልደ ገብርኤል የተባሉ ምሑር፤ «ዘ ኢኮሎጂ ኦቭ ሔልዝ ኤንድ ዲዝዝ ኢን ኢትዮጵያ» በሚል ርእሰ በጻፉት መጽሐፍ እንዳቀረቡት፤ ኢትዮጵያ የግብርና አገር ብትሆንም፣ ከሕዝቧ **86%** የሚሆነው ገበሬ መሆኑ ቢረጋገጥም፣ ሀገሪቱ በማንኛውም ጊዜ ሊታረስ የሚችል **15.8** ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንዳላት ቢታወቅም፣ **69** ሚሊዮን የቀንድ ከብት፣ **62** ሚሊዮን ዶሮ ቢኖራትም፣ እድገቷ ዝቅተኛ በመሆኑ እያንዳንዱ ሰው በቂ ምግብ አያገኝም፡፡

ይህም የሆነው እርሻው የሚታረሰው ኋላቀር በሆነ ዘዴ በመሆኑ፣ በክምችት ወቅት በሚደርሰው ብክነት፣ በቂ የመጓጓዣ አገልግሎት ባለመኖሩ፣ ስለጤንነት ጉዳይ ትምህርት ባለመሰጠቱ፣ ስለ አመጋገብና ስለ ቤተሰብ ቁጠባ ባለማወቅ፣ በአንድ በልምድ በተመረጠ እህል ላይ የተመሠረተ አመጋገብ ጋር የሙጥኝ በማለት፣ በተላላፊ በሽታዎች መስፋፋት፣ ምግብ ለመግዛት አቅም በማጣትና ድርቅ በመኖሩ ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ችግር ለማስወገድ ጥረት የተደረገ መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች ቢኖሩም ውጤቱ የሚያረጋግጠው ግን ለመፍትሄነት አለመብቃቱን ነው፡፡

ይሁንና የኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በድርቅ አደጋ የመጠቃት፣ ከዚህም የተነሳ ሕዝቧ ለረሃብና ለእርዛት የመጋለጡ ጉዳይ በእርግጥ የማይፈታ እንቆቅልሽ ነው**?** ሁኔታዎች ከተመቻቹለት **85** በመቶ የሚሆነው ገበሬ፣ ራሱን ችሎ **15** በመቶ የሚሆነውን ሕዝብ መደገፍ ይሳነዋልን**?** ብለን መጠየቃችን አልቀረም፡፡ ነገሩ በጣም ውስብስብም ነው፡፡

በመሠረቱ ያለፈውንም ሆነ ያለውን ስርዓት በየምክንያቱ እየኮነንን መኖር ብቻውን የትም አያደርሰንም፡፡ ሥር የሰደደው ችግራችን የተከሰተው ደጋግሞ በሚያጠቃን ድርቅ ምክንያት ነው፡፡ የአስተራረስ ዘዴያችን በጣም ኋላ ቀር በመሆኑ ነው፡፡ **85** በመቶ ገበሬ ያለጥርጥር **15** በመቶ የሆነውን ሕዝብ መመገብ ይችላል የሚል ሒሳባዊ ስሌትን መሠረት ያደረገ አመለካከት በመስፈኑ ነው፡፡ ይኸው **85** በመቶ ገበሬ እንኳንስ ተጨማሪ **15** በመቶ የሆነ ሕዝብ ሊቀልብ እራሱንም ቢሆን ከርሃብ አላዳነም፡፡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ፣ የነጻ ኢኮኖሚ ሥርዓትን የተከተለ አሠራር ይተግበር የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

በመሠረቱ የኢትዮጵያ የግብርና ኢኮኖሚ ደካማ በመሆኑ ሕዝቡ በተደጋጋሚ ለረሀብ ይጋለጣል፣ ሲባልም ሆነ የዕለት ምግቡ ከአማካዩ ዝቅተኛ ካሎሪ እንኳን ያነሰ ነው ሲባል የአንድ ዓመት ወይም የሶስት አራት ዓመታት ችግር ውጤት ሳይሆን ከዚያ በፊት የነበሩት ሃያና ሰላሳ ዓመታትንም የሚዳስስ ነው፡፡

ችግሩ ይህ ከሆነ ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚመለከታቸው ሁሉ የተዘራው እህል በደንብ እንዲታረምና በየእርሻው መሃል ውሃ የሚቋጥር መሬት እየተተለተለ እንዲዘጋጅ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ዘሩን ተባይ እንዳያጠፋው በልዩ ልዩ መንገዶች መከላከል፣መሬቱን ውሃ እንዳያጥበው ገበሬው ነቅቶ እንዲጠብቅ መምከር፣ ዘሩን አፈር ማሳቀፍና ማዳበሪያ መጨመር ያስፈልግ እንደሆነ አቅም የሚፈቅደውን ነገር ሁሉ ማድረግ ሁኔታው ያስገድዳል፡፡ ውርጭ እንዳይመታው ለመከላከል በማንኛውም ጥረት መሞከርና ሌሎችም የአካባቢ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለመጠቀም ግንባር ቀደም ዝግጁነት ያስፈልጋል፡፡ ምርቱ ከመድረሱ በፊት እንዳይታጨድ ወይም ጊዜው እስኪያልፍ ድረስ እንዳይጠበቅ፤ ሲከመር ሲወቃና ሲሰበሰብ እንዳይዝረከረክ እስከ መጨረሻው ክትትል ማድረግ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

አገሪቱ ሰፊ የለማ መሬት ስላላት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ኢንቨስተሮች ሀብታቸውን በዚህ የኢኮኖሚ መስክ ላይ እንዲያውሉ የበለጠ አመቺ ሁኔታን መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አመራር ብሔራዊ ፖሊሲ መነደፍ መሠረታዊ ምክንያት ሕዝብ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሠራሽ ችግሮች ምግብና ሌሎችንም መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ማሟላት አቅቶት ኑሮው እንዳይናጋ በመሆኑ፣ ይኸው የተቀደሰ ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድ ፖሊሲውን በትክክል እንዲያስፈጽሙ ኃላፊነት የተጣለባቸው ክፍሎች ሁሉ በንቃት ሊታትሩ ይገባል፡፡

እስካሁን ሕዝብ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት ሲያልቅ የነበረው አገሪቱ አቅም ስላልነበራትም ሆነ ባይኖራትም እንኳን የእርዳታ እጁን የሚዘረጋላት የዓለም በጎ አድራጊ ማህበረሰብ አጥታ አይደለም፡፡ ነገር ግን አቅሟን አቀናጅታ እንዴት እንደምትጠቀምበት ስልት ባለመነደፉ፣ ከልማት ጋር ባልተያያዘ መልኩ እርዳታ ሲሰጥ ስለነበረ ነው፡፡

እያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ ግንኙነት ካለው ሌላ ዘርፍ ጋር ሊያሠራ የሚችል ፖሊሲ ከተቀየሰ በእርግጥም የአንድ ዓመት ችግር ቀርቶ ምንጊዜም ቢሆን ሰውና ተፈጥሮ የሚያደርሱብንን ችግር ለመቋቋም እንችላለን። ዛሬ በቂ ምግብ ተመግበው የሚያድሩ አገሮች ሁሉ እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱት ተክክለኛ የኢኮኖሚ አቅጣጫ በመቀየሳቸው ነው፡፡